ታህሳሥ 5 1998 ዓም ( ዲሴምበር 7 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## ማመፅ ወይስ መጎንበስ

አንድ ሕዝብ በታሪኩ በሁለት ወሳኝ አማራጮች መሀል አቋም መውሰድ የሚገደድበት ወቅት እንዳለ ከራሳችንም ተመክሮ የተገነዘብነው ጉዳይ ነው:: በዚህም ጊዜ የሚደረገው ምርጫ በሀገርና በወገን የነገ ዕጣ ላይ ረጅም አንደምታን አስከትሎ ይከሰታል:: መቆጨቱ አያዋጣም፤ ላለፈ ክረምት ቤት ሥራ፤ ለፈሰሰ ወተት እንባ ማፍሰስ ይሆናል:: አይበጅም:: ለዚህም ነው በወሳኝ አማራጭ ጊዜ ትክክለኛውን አቋም መምረጡ አስፈላጊና የሞት ሽረት ጉዳይም ነው የሚባለው::

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያና ሕዝቦቿ የነገ ዕድል በዚህ ዓይነት አማራጭ ወይም አጣብቂኝ መሀል ይገኛል:: ሕዝቡ በቃኝ ለጨቋኝ ቡድን አልገዛም ብሎ ድምፁን ለተቃዋሚ ኃይሎች በመስጠት ድልን ለግሷቸዋል:: ገዢው ቡድን ደግሞ እንደተጠበቀው የሕዝብን ድምፅ ረግጦ፤ ራሱን አሸናፊ ብሎ ሊገዛ በግፉ ሊቀጥል እየሞከረ ነው:: ለሕዝብ ያለው አመራጭ ድምፄ ይከበር ብሎ በፅናት መቆምና ማመፅ ወይም ለወያኔ ዛ ተሸናፊ ሆኖ የመለስን ቡደን የበላይነት መቀበል ነው:: ወይ ባርነት ወይ ነፃነት:: መብትን ተነፍጎ ተጎንብሶና ተቀይዶ መኖር ወይም ማመፅና በዚህም ሰብዕናንም መብትንም ማስከበር:: የመሀል መንገድ የለውም:: አምስት ዓመት ጊዜ ሰጥቶና ጠብቆ የሚመጣ ሌላ ልዩ ምርጫም የለም:: ከመንታ መንገድ ደርሰናል--ከኋላም ጥርሱን አግጦ ሊውጠን÷ ሊሰለቅጠን የሚያጓራ ሰው በላ ሥርዓት አለ :: ጊዜ የለንም::

የመለስ አገዛዝ የሕዝብን ድምፅ ረግጦና አጭበርብሮ ራሱን አሸናፊ ብሎ ደምድሟል:: ረባ አልረባ ተቃዋሚ ኃይሎች የለገሱትን የመውጫና ራሱን የማዳኛንም አማራጭ አልቀበልም ከማለቱ ሌላ በእሱ ብሶ ከማንም ጋር በጥምር መንግሥት አልያያዝም ብሎ ደንፍቷል:: የበላይነቴን ተቀበሉኝ አለበለዚያ የአፈና ቡጢዬ ያዳሽቃችኋል ነው እያለን ያለው:: ይህን ፈርቶና የጨቋኙና አፋኙን ቡድን ድንፋታ ተቀብሎ በወያኔ ፓርላማ መኮልኮል ከተከተለ÷ እውነትም የመለስ ድንፋታ ውጤት አስገኝቷል ማለት ነው:: ይህም ምርጫ ማለትም የእነ መለስ ዜናዊን የበላይነትና አሸናፊነት የመቀበሉ ምርጫ ደግሞ የባርነትን ቀንበር መምረጥ መሆኑ ግልፅ ነው:: ለሕዝብ ያለው የስርየትና የሀርነት ምርጫ ግን÷ የአገዛዙ አሸናፊነት አልቀበልም ማለት፤ የሕዝብ ድምፅ ይከበር ብሎ መፅናትና መቸም ቢሆን መቸ ÷ የመጣ ቢመጣ ለአገዛዙ አለመጎንበስ ነው:: ሌላ አማራጭ የለም:: ሕዝብ የሚፈልገው ምርጫና አቋም ይህ ብቻ ነው:: ይህ ደግሞ÷ በጫካ ታሪኩ በፍርሀትና ሽሽት ለፍርድ ቀርቦ የነበረውና ዛሬ በቤተ መንግሥት ግምብ ክልል ደፋር ነኝ ሊል እያቃጣ ያለው መለስ ዜናዊ አለ እንደተባለው ለጫካ፤ ለስደትና ለእስርም ሊዳርግ የሚችል ነው:: ለየትኛው የሚለውንም ታጋዩ ክፍል በጊዜ አጢኖ ተገቢውን እርምጃ ወይም መከላከያ መውሰዱ ይጠበቅብታል::

ምርጫ አለ ስንል እንደ እውነቱ ከሆነ÷ ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ነው:: ሕዝብ እንደ ሕዝብ ጭቆናና ባርነትን ሊመርጥ፤ ሀገር አጥፊን ቡድን ገዢ ብሎ ሊቀበል ከቶም የሚታሰብ አይደለም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ በወያኔ ላይ አምርሮና ቆርጦ

የተነሳ በመሆኑ፥ ወደ ኋላ የሚመለስ አይደለም። ተቃዋሚ ኃይሎች አንድነታቸውን መጠበቅ አቅቷቸው፤ በአገዛዙ ተሸንፈው፤ የሕዝብን ሳይሆን የራሳቸውን ውሱን ጥቅም አስቀድመው ለመለስ ቡድን እጅ ቢሰጡ እንኳን፥ ሕዝቡ በቃ ብሏልና የአገዛዙ ዕድሜ በረጅሙ ሊቀጥል የሚችል አይሆንም። ወድቀቱ ጀመሯል፤ ግበዓተ መሬቱ ደግሞ ነገ ካልሆነ ተነገ ወዲያ ቀጣይ ነው። ይህ በእርግጠኝነት የምንናገረው ሀቅ ነው።አ

ሕዝቡ በትግሉ ድሉን ያረጋግጣል ስንል ደግሞ በምን ዓይነት ትግል የሚለውን ወሳኙ ወያኔ ሳይሆን በደል ተቀባዩ ሕዝብ ነው። በአሁኑ ጊዜ ተቃዋሚ ኃይሎች ከሞላ ጎደል በሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ ስልት እንታገላላን ብለው ተስማምተዋል ማለት ይቻላል። መንገዱ ጠቦብናል ብለውና አማራጭ ያለን ይህ ብቻ ነው ብለው ብረት ያነሱ ያሉ ሲሆን፥ ለዚህም በቅድሚያ ተጠያቂው በሰላምና በህጋዊ መንገድ መብታቸው ተጠብቆ ድርጅቶች እንዳይታገሉ ጋሬጣ የሆነው የመለስ ቡድን ነው። ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ ስንል አንዳንዶች እንደሚያደርጉት በአብላጫው እጅን እግርን አጣጥፎ በመቀመጥ የባዕዳንን ጣልቃ ገብነትና አማላጅነት መጠበቅ ማለት አደለም። እራሳችንን ከጭቆና ለማላቀቅ ከራሳችን የበለጠ ኃይልና ወሳኝ የለም ማለታችን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት አስራ አራት የመከራ ዘመን ለሰላሙ ክብደትና ቅድሚያ በመስጠት እስከ መጨረሻው ምዕራፍ ድረስ ቢጓዝም መለስና ባልደረቦቹ ሊበገሩ አልቻሉም። ነፃነቱን ለማስከበር ሕዝቡ ሌላ መንገድ እንዲፈልግ እየተገደደ ነው። አዲስ የትግል ምዕራፍ ለመክፈትም ሁኔታው እያስገደደው ይገኛል።

ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ በዋና ደረጃ አመፅ ነው። እምቢ አልገዛም፤በቃኝ አሻፈረኝ ማለት ነው። የአገዛዙ ህግ ሥርዓት አክበሮ የሚካሄደ ሳይሆን፥ የአገዛዙ ህጎች ጥሶና አልከተልም አላከብርም ብሎ መነሳት ማለት ነው። አገዛዙ የሕዝብን መብት ረግጦና ህግን አላከብር ብሎ እየቀጠለ ባለበት የእሱን ኧግረ ሙቅ ህጎች ሕዝብ እያከበረ ትግል ሊያከሂድ የሚጠበቅ አይደለም። ማህታማ ጋንዲ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግ፤የሶዌቶን ከደቡብ አፍሪካ ወዘተ ከባዕድ፤ የራሳችን የየከቲት ቡቃዮች በ1966፤ ሕዝባችን በሰኔ 1997 ያሳዩንም ይህንኑ ነው። የመለስ ዜናዊን አዋጅና ህግ ተከትሎና አክብሮ ለመብት ሊካሄድ የሚችል ትግል የለም። ሰልፍ ሲከለክል እገዳውን አልቀበልም በማለት፤ ያቀደውን በመሻጠር፤የኤኮኖሚ ማዕቀብ በንግድ ተቋሞቹ ላይ በማካሄድ ወዘተ መታገል ያሻል ማለት ነው። ይህ ሕዝባዊ አመፅም ሰላማዊ ስለተባለ ብቻ፥ መስዋዕትነት የመከፈልበት አይደለም ብሎ ማሰብ ደግሞ ከባድ ስህተት ነው። ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ ብዙ መስዋዕትነትን ይጠይቃል።

ባለፈው ሰኔ ሕዝብ የከፈለው የደም ዋጋ አልበቃ ብሎ ይኸው በመስከረም ወር ደግሞ የብዙ ንፁህ ዜጋ ደም እንደጎርፍ በየቦታው ፈሰሰ። ከዚያም በፊት 14 ዓመት ሙሉ ሲታገሉ የተሰዉት የሀገር ልጆች ቁጥራቸውን በውል ማወቅ አልታቻለም። ። በሰላም ታግለው ለዓመታት ለእስር የበቁት፤በእስር ላይ የሞቱት ጀግኖች ምሳሌ ናቸው። ከሀገራቸው ተፈናቅለው ለስደትና ለመከራ የተዳረጉት ምስክሮች ናቸው። ልጆቿ በአግአዚያን ነፍሰ ገዳይ ቦድን ተረሽነውባት ባዶ ቤት የታቀፈች እናት ምስክር ናት። ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ የደም ዋጋን ይጠይቃል። ለዚህም ነው ከመቸውም ጊዜ በበለጠ የቆረጡና ትግሉ ነው ህይወቴ፤በትግል መሞት ህይወት የሚሉ ጀግና መሪዎች የሚያስፈልጉት። ይህ ደግሞ የሚቀር አይደለም!

ሰላማዊ ስለተባለና ብረት ሰላልተነገበ ግብገብና የሞት ሽረት ሁኔታ የለም ማለትም አይደለም። ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ፀጉሩ የታጠቀና አፋኝና አረመኔን ኃይሎችን ያሰማራን አገዛዝ በባዶ እጅ መጋፈጥ ቀላል አይደለም። ሲናገሩትና፤ እንዲህ ነው እንዲያ ነው ሲሉት ቀለል ያለ ቢመስልም የቁርጡ ቀን ሲመጣ የፎከረው ሁሉ በቦታው ይገኛል ማለትም አይቻልም። ይህ የትግል ስልት ከበድ ያለ ወኔን ጠያቂ ነውና ለዚህም ተዘጋጅቶ መገኘትን ይግድ ይላል። ከጫካው ውጣ ውረድ፤ ከተባዩና ረሀቡ የተራቀ ቢመስልም፥ የሰላማዊው ትግል ሸክም ራሱ ቀላል አይደለም። ይህን ሸክም ግን ቀላል የሚያደርገው ወሳኝ ጉዳይ ሕዝብ በጋራ አመፅ መነሳቱ ነው። ታጋዮች ብቻ ወይም ድርጅቶች ብቻ የተሰማሩበት በሆነ በጣም ባስቸገረ ነበር። ሕዝብ ግን አምርሮና ለመስዋዕትነት ዝግጁ ሆኖ ምሩን አታግሉን ካለ የዚህ ትግል ሸክም የቀለለ ይሆናል። ለዚህም ነው የድርጅት መሪዎች ፅኑ ሆነው ሕዝባዊ አመፁን ሊመሩ የሚጠበቀው። ደርጅት የሕዝብ የትግል መሳሪያ ካልሆነ ፋይዳው አጠያያቂ ነውና የመሪዎች ሚናም በዚሁ ለድርጅት በምንሰጠው የሕዘብ አገልጋይነት ላይ የተገነባ ነው።

አገዛዙ ወይም መንግሥት ተብዬው ኃይል አለው ሕዝብ ግን ኃይል አልባ ነው የሚለው የተለምዶ አቋምና አስተሳሰብ ከመሠረቱ የተሳሳተ መሆኑን በትግላችንም ያሳየነውና የሌሎችም ትግል ያስመሰከረው ሀቅ ነው። ኃያል ነን ያሉት ሁሉ በሕዝብ ትግል ተንኮታክተዋል። ይህ የሆነበትም ዋና ምክንያት፥ ታሪክ ሰሪ ጉልበት የሕዝብ ብቻ በመሆኑ ነው። ዛሬ የሚያቃጭለውን የመለስ ዜናዊ የቀቢፀ ተስፋ ዘቻና ድንፋታ ትላንት ቀይ ቀለም የተሞላ ጠርሙስ እየሰበረ ኮለኔሉ ሲያጓራ የሰማነው ዓይነት ነው። ቀቢፀ ተስፋ። ሕዝብ ከተነሳ የሚገታው ማንም ኃይል የለም። ማመፁ ኃይሉ ነው። በጋራ መነሳቱ አየበገሬ የሚያደርገው ነው። መጎንበስ በቃ ማለቱ ጉልበቱ ነው። ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ የዚህ ኃይል አንጻሩ መከሰቸው በመሆኑም አሻናፊነቱ የሚያጠራጥር አይሆንም። ደግመን ደጋግመን አንጻቀረብነውም ይህ ትግል ብዙ መልክ አለው። በዋና ዋና የህብረተ ሰቡ ብሶቶች ዙሪያ ሰለማዊ ሰልፎችን ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት ድምፅ ሰረቃውን በማቀወም የመለስን አሸንፌያለሁ ጩኸት ባለመቀበል የተቃውሞ ሰልፍ ማደርግ ይቻላል። በሁሉም ቦታዎች። ሰልፍ ሲከለከል እምቢ መብታችን ነው በሰላም መቃወም ብሎ መሰለፍ ማለት ነው። እዚህ ላይ ታዲያ የሕዝብ ድርጅት ነን የሚሉቱ በጉዳዩ የለንበትም ብለው ማማል መገዘት ሳይሆን፥ አለንበት ወደፊትም ሌሎች ስልፎች ማደራጀትና ማከሄድ መሠረታዊ መብታችን ነው ብለው መቆም አለባቸው ማለት ነው።

ከሰልፍ በሻገር ደግሞ የሥራ ማቆም አድማ፥ ዓይነታ መሳሪያ ነው። ገዢውን ክፍል ሊያንበረክክ የሚችልም ነው። ይህም ፈቃድ አያሻውም፤ በእነ መለስ ፍቃድም ሊካሄድ የሚችል አይደለም። የተናጠሉ አድማ ቦታውን ለጠቅላላ አድማ ከለቀቀ ደግሞ የመለስ አገዛዝ መሽመድመዱ የሚታይ ይሆናል። በገጠር ደግሞ ግብር አንከፍልም ዓይነት እምቢታዎችም ሊደራጁ ይችላሉ። በኤኮኖሚው መስክ በሶዌቶ ደቡብ አፍሪካ እንደተደረገው ሁሉ፥ በሀገር ውስጥም ሆነ ባዕድ የወያኔ የሆኑ ወይም የአገዛዙ ደጋፊዎች ንብረት በሆኑ የ ግድ ተቋሞች ላይ ማዕቀብ ማድረግ ይቻላል። ከእነሱ አለመግዛት፤አለመገበያየት። የአገዛዙ አጫፋሪ የሆኑትን ቀንደኛ ግለሰቦች ከህብረተ ሰቡ ማግለል። ባዕዳን አገዛዙ የሚረዳ እርዳታ እንዳይሰጡ መቀስቀስ። ለአገዛዙ ገቢ ሊሆን የሚችል ወጪን በተመለከተ ተገቢውን

የማቀብ እርምጃ መውሰድ:: ጎራን መለየት:: በሕዝብ መድረክና ስብሰባ ወይም በዓል የአገዛዙ ተወካዮች ከቶም ዝር እንዳይሉ ማድረግ:: የቤት ኪራይ አንከፍልም፤ የመብራትና ወሀ ግብር አንከፍልም ወዘተ ብለው ደቡብ አፍሪካውያን ያካሄዱት ትግል ምሳሌ ነው:: በማዳጋስካር ደግሞ ምርጫውን አሸንፌያለሁ ብሎ የደረቀውን ገዢ ቡድን አንታዘዝልህም ብሎ ሕዝቡ እንዳሸነፈውም ማስታወስ ይጠቅማል:: መቸስ ማል ጎደኒ ወይም ምን ማድረግ ይቻላል በሚል ሸንፈተኛነት እጅን ለመለስ ቡድን መስጠት ሳይሆን፥ ወይም በበላይነት በሚጫወትበት ፓርላማ ተብዬ ኦና ገብቶ ለመገኘት ሳይሆን፥ ከሕዝብ ጎን በአመፁ ጎራ መገኘት-መቅደም መመረጥ አለበት ማለት ነው::

አልገዛም ብሎ፤እምቢ ብሎ መፅናት ፍትሀዊ ትግል እንጂ አንዳንዶች እንደሚሉት፥ ስልትና ዲፕሎማሲያው ችሎታ ማነስ አይደለም:: በአሁኑ ጊዜ የመለስ ቡድን፥ የሕዝብን ድምፅ ሰርቆ ባለበት ይህንን በሆነ ምክንያት መቀበል ተገቢ አለመሆኑ ግልፅ ነው:: የሕዝብ አቋም ደግሞ ምን መሆኑን ማወቅና ይህንንም መከተል ከድርጅቶች የሚጠበቅ ነው:: ሊደመጥ የሚገባው፥ ማለትም የድርጅት መሪዎችን ሊያሳሰብና ውሳኔያቸውንም ሊቃኝ የሚገባው የሕዝባችን ድምፅና ፍላጎት ነው:: ባዕዳን የሚሰጣቸው ቦታ ከዚህ በኋላ የሚመጣ መሆን አለበት::  በአሁኑ ወቅት እንደታዘብነውም  የአሜሪካና የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች የመጀመሪያ ጭንቀታቸው ሎሌያቸውን የመለስን ቡድን ማዳን ነው:: ድርጅቶች ከሕዝብ ጋር ሰምረው ከተነሱና ካመፁ ያሁኑን ሁኔታ ታምራዊ በሆነ መልኩ ሊለውጡት ይችላሉ:: ደጀናቸው በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ነውና:: የመለሰ ቡድን ከሕዝብ ዘርፎ ባገኘው ገንዘብ፥ የገዛው መሳሪያ ኃይል ሊሆነው ወይም ከውድቀቱ ሊያድነው አይችልም:: የሚችል ቢሆንማ ኖሮ ቀደም የነበረው አገዛዝም ባልወደቀ ነበር:: ኃያል መንግሥት ፈቃዱ ስለአልሆነ ተብሎ ያለ  እርሱ ትዕዛዝ  የሚሆን  ነገር የለም ብሎ የሀገርን ዕጣና የሕዝብን መብት አሳልፎ መስጠቱም ጥፋት ነው:: በታሪክም የሚያሳፍር ድርጊት መፈፀም ነው::

ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ ፍቱን የትግል መንገድ ነው እስከተባለ ድረስ፥ ይህ ስልት የሚጠይቀውን ለማሟላት ደግሞ፥ ቢያንስ በቅድሚያ የዚህን አጥር የሚተክለው አገዛዙ ሊሆን እንደማይችል ማወቅ ያሻል:: የሰላማዊው ትግል መንገድ በሾህ ከታጠረ ደግሞ ሕዝብ ሌላ አማራጭን መውሰዱ የማይቀር ነው:: የዚህ መዘዝ ደግሞ ከከፋ፥ ተጠያቂውና ተጠቂው ራሱ ወያኔ መሆኑ ግልፅ ነው:: ትግሉ ስልታዊና ሙያተኛ መሆን አለበት የተባለውንም መርሳት ስለማይገባ አገዛዙ እያካሄደ ያለውን ከፋፋይ ዘመቻ በመቋቋም፤ የጦር ኃይሉ ከሕዝብ እንዲወግን በመቀስቀስ፤ የትግራይ ተወላጆችን ከጎኑ ለያሰልፍ እያካሄደ ያለውን መሰሪ ጥረት በማከሸፍ፤ ጠበትንም ትምክህትንም በመራቅ የሕዝብን መብትና አንድነት በማስቀደም መታገል ያስፈልጋል:: ቀደም ብለን ሕዝብን ማዳመጥ ስንልም የእኔ ብጤውን ሰርቶ አደሩን ያገለለ የሕዝብ ቀመርን ሳይሆን፤ ባለሀብትና ተማረ የተባለውነም ብቻ የሚያዳምጥ ሳይሆን ሰፊ ሕዝበ  የተባለውን ከተሜወንና የገጠር ነዋሪውን፤ወጣት ሽማግሌውን፤ ሰርቶ አደሩን ሥራ አጡን፤ወንድ ሴቱን፤ክርስቲያን እስላሙን ማለትም ሁሉንም ኢትዮጵያዊ፤የዚችን ሀገር ዜጋ ማዳመጥ ማለታችን ነው::

ኃይል የሕዝብ ነው:: ሰልፋችን ከሕዝብ ጋር ከሆነ ኃያል እንሆናለን:: በማመፅ ፈንታ ሰበቦች ደርድረን የመጎንበስን፤የእጅ መስጠትን ማላ ተብዬ ቅሌት

ከተቀበልን ደግሞ ታሪክና ሕዝብ ከመታዘብም ሌላ አንቅረው ይተፉናል ማለት ነው፡፡ ይህን ሀቅ ድርጀቶች መቀበል አለባቸው፡፡ ዛሬ ሊሞት ሲል የመለስ አገዛዝ ጠባዩን ሊለውጥ አይችልም፡፡ አደብ አይገዛም፡፡ ተው ሲሉት አይተውም፡፡ በተቃኘበት ፀረ ሕዝብ ፀረ ኢትዮጵያ ጎዳና ይነጉዳል እንጂ ገደሉም ጥፋቱም ታይቶት አይታረምም፡፡ የመለስ አገዛዝ በሕዝብ ድምፅ ከሥልጣን ተወግዷል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ነው የተቃዋሚ ኃይሎች ግዴታና ሥራ፡፡ ለዚህም መንገዱ ዕብሪት ያደነቆረውን አገዛዝ ልምምጥ ሳይሆን፥ ሕዝብን አቅፎ ታሪካዊና አርድ አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመፅን ማካሄድ ነው፡፡ ሌላ አማራጭ የለም--ባርነትን፤ ሀገር ማጣትን አማራጭ ነው ብለን በመውሰድ በጅግኖች ደም የተፃፈውን ታሪካችንን ልናበላሽና ልናረክስ ካልሆነ በስተቀር፡፡ ይህን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ መቸም አይቀበለውም፡፡ በበኩላችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ድልን ሳይቀናጅ ትጥቃችን እንፈታለን፥ ትግላችንን እናለዝባለን ማለት   ዘበት ነው፡፡